**የተያዘ (የዘገየ) በረከትን ማስለቀቅ፤**1 ሳሙ 1፡1-18

ህልቃና ከሌዋውያን የዘር ሀረግ የመጣ መሆኑን 1ዜና 6፡1-16-26-28-33-34 ያስረዳል፡፡ እርሱም ኤፍሬማዊ ሲሆን የሚለው (ከዮሴፍ ልጆች አንዱ በሆነው) ለኤፍሬማውያን በተመደበ ድንበር ውስጥ፣ ለሌዋውያን በተከለለ አርማቴም መሴፋ በሚባል ከተማ/አካባቢ የኖረ ስለሆነ ነው፡፡ (ሌዋውያን ከእስራኤል ነገዶች ጋር ርስት ያልተሰጣቸው (ያልነበራቸው) ሲሆን ይኖሩ የነበሩት በመላው እስራኤላውያን ነገዶች መካከል ተበታትነው በሚገኙ 48 ከተሞች ውስጥ ነበር፡፡ አርማቴም መሴፋ ከእነዚህ ከተሞች ውስጥ አንዱ ሊሆን ይችላል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ዘሁ 35፡1-8, እስራኤላዊያን ከነዓናዊያንን ተዋግተው ከወረሷቸው ስፍራዎች በኢያ 21፡4-5፣ 21-22 ለኤፍሬማዊያን ከተመደበው ርስት ለሌዋዊያን የተሰጡ ስፍራዎች መኖራቸውን ያስረዳል፡፡

ሕልቃና አንዲቱ ሐና፣ ሌላይቱ ፍናና የተባሉ ሁለት ሚስቶች ነበሩት፡፡ ፍናና ልጆች ሲኖሯት ሐና ግን ምንም ልጅ አልነበራትም፡፡ እርሱም ሁሉን ቻይ ለሆነው ለእግዚአብሔር በየዓመቱ ከቤተሰቡ ጋር ወደ ሴሎ ሄዶ የሚሰግድና መስዋዕት የሚያቀርብ ሰው ነበር፡፡

እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር እያንዳንዱ ሰው ሊኖረው ይገባል ብሎ የመደበው መልካም ነገር አለ፡፡ ከእነዚህም ነገሮች መካከል አንዱ ዘፍ 1፡27፣ 2፡18፣ 24 ነው፡፡ ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለምና የሚስማማውን ረዳት አበጅለታለሁ አለ፡፡ እንዳለውም አንድ ረዳት አበጅቶ ሰጠው (ማቴ 19፡8፣ ሚልክ 2፡15፡፡) የወንድና ሴት መጋባት ሥርዓትና ብዙ ተባዙ ብሎ ልጅ መውለድም የሰጠው እርሱ ነው፡፡ ከአንድ ሚስት በላይ ማግባት በብሉይ ኪዳንም የተፈቀደ አልነበረም፡፡ ሕልቃና ያውም ሌዋዊ ሆኖ ሁለት ሚስት ያገባው ምናልባት መጀመሪያ ሐናን አግብቶ ልጅ ሳትወልድ ስትቀር ፍናናን ደግሞ ሊሆን ይችላል ተብሎ ይታሰባል፡፡

በሁለቱ ሴቶች መካከል የተፈጠረው አለመስማማት ዋናው መነሻ ምክንያት እግዚአብሔር የሰጠው የአንድ ለአንድ ጋብቻ ስርዓት በመጣሱ ነበር፡፡ ከአንድ በላይ ሴት ማግባት የግጭት መንስኤ ሆኖ የሚታየው በህልቃና ቤት ብቻ ሳይሆን በአብረሐምና በያዕቆብ ትዳርም ውስጥ የሳራና የአጋር፣ የልያና የራሄል አባታቸው ላባ ለያዕቆብ 2ቱም ልጆቹን በመዳሩ ፍጭት ፈጥሯል፡፡ የትዳር መስራቹ እግዚአብሔር ሲሆን ጸንቶ መቀጠል የሚያስችለው መሰረቱ ደግሞ በእውነተኛ ፍቅር ላይ የተመሰረተ ታማኝነት ነው፡፡ የሐናና ፍናና አለመስማማት የሁሉም ቤተሰብ ሰላም የሚነካ ጉዳይ ቢሆንም ዋናዋ ተጎጂ የነበረችው ግን ሐና ነበረች፡፡

1. ለሐና ልጅ አልባ መሆን የእያንዳንዳቸው እይታ/ምላሽ ምን ይመስል ነበር?

**ህልቃና**፡- በጊዜው ብዙ እስራኤላውያን እግዚአብሐርን መከተል ቸል ያሉበትና በተለይ ክፉ ስራ የሰሩ አፍኒና ፊንሀስ የተባሉ የካህኑ ኤሊ ልጆች የክህነት ስራ እግዚአብሔር የጠላበት ጊዜ ሆኖ ሳለ ህልቃና እግዚአብሔርን በመፈልግ እነርሱ ወደነበሩበት ሴሎ መሄዱ ትልቅ ነገር ነው፡፡ ሐናን ይወዳታል፤ ፍቅሩን ለመግለጽና ለማጽናናት ሲል መስዋዕት በሰዉበት ስፍራ ለቤተሰቡ ምግብ ሲያከፋፍል ለርሷ እጥፍ ድርሻ ይሰጣት ነበር፡፡ ስታዝንና ስታለቅስ ከአስር ወንዶች ልጆች እኔ እበልጥልሻለሁና (ይበቃሻል) አትዘኚ፣ አታልቅሺ (ዝም በይ) በማለት ለማጽናናት ሞክሯል፡፡ ግን ለገጠማት የመካንነት ችግር ይሄ ነው የሚባል የመፍትሄ እርምጃ ስለ መውሰዱ የተመዘገበ ነገር የለም፡፡

**ፍናና**፡- ሐናን ለማበሳጨት የምትጠቀመው የጎደላትን በማሳየት፣ "አንቺ መካን" ብላ በመጥራት ሊሆን

ይችላል፡፡

- ለእርሷ ልጆች ስላላት ለመታበይ መነሻ ሆኖዋታል ማለት ይቻላል፤ ህልቃናም ዝም የሚላት ልጆች ስላላትና ስለምትወልድለት ሊሆን ይችላል፡፡
- ሃናን መተንኮሷ በተለይ የሚጎላው ከህልቃና ጋር በያመቱ ለእግዚአብሔር ለመስገድና መስዋዕት ለማቅረብ ወደ ሴሎ ሄደው በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ መስዋዕት በሚቀርብበት ጊዜ መሆኑ የከፋ ያደርገዋል፡፡
- ይህን ለማድረግ የሚያነሳሳት ምክንያት፣ ህልቃና ከእርሷ አብልጦ የሚወዳትና እጥፍ ድርሻ ይሰጣት ስለነበር ከመቅናቷ የተነሳ፣ ትዳርዋን ጥላ እንድትሄድላት የምታደርገው ይመስላል፡፡

**ሐና፡-** ባለቤትዋ ይወዳት የነበረው መልኳ/ቁመናዋ ከሌላዪቱ የተሻለ ስለሆነ ወይም ባህሪዋም መልካም ስለነበረ ወይም ሁለቱም በጥምር ስለነበራት ሊሆን ይችላል፡፡
- ሐና በባለቤትዋ እንድትወደድ ባደረጋት የእግዚአብሔር ስጦታዋ/ባህሪዋ ወይም በሚወዳትና ለእርሷ በሚያደላው ባለቤትዋ ተመክታ/ታብያ ሌላዋን ስትበድል አልታየችም፡፡ (እግዚአብሔር በሰጣት መልካም ነገር ምክንያት መታበይም ሆነ ኩራት አላሳየችም)፡፡
- ለፍናና ልጆች ስለነበራት በቅናት በመነሳሳት ያደረገችው ክፉ ነገር የለም፤

- ከቤተሰቡ ታሪክ አንጻር ሐና በጣውንቷ ሰበብ እየፈለገች ጠብ የምታነሳ አልነበረችም፡፡ ከቤተብ ሁሉ ጋር በሰላም የምትኖር፣ ክፉን በክፉ መመለስ ያልታየባት ሰው ነበረች፡፡

- ካህኑ ኤሊ አለ ጥፋቷ ሲገስጻት የሰጠችው አስደሳች መልስ መልካም ባህሪ የተላበሰች እንደ ነበረች የሚያሳይና በሰውም ሆነ በእግዚአብሔር ፊት የሚያስመሰግናት ነው፡፡

- ፍናና ብትበድላትም ምንም የበቀል እርምጃ አልወሰደችባትም፡፡ ባለቤትዋም ከፍናና ጠበኝነት ስላላዳናት ያደረገቸው ነገር/የወቀሰችበት ጊዜ የለም፡፡ እግዚአብሔርም ልጅ ባልሰጣት ጉዳይ ስታማርር አልታየችም፡፡

- ሐና ያስለቅሳት፣ ያሳዝናትና ያስመርራት የነበረው ዋናው ምክንያት ጣውንቷ ልጅ ባለመውለዱ ትተነኩሳት ስለነበር ነው፡፡ የጣውንቷ ትንኮሳ እንድታስታውስና እንድታለቅስ የሚያደርጋት በዚያ ዘመን ልጅ አለመውለዱ የሚያስከተላቸው ውጤቶች የሚከተሉት ስለ ነበረ ሊሆኑ ይችላሉ፡ -

  - የሴት ልጅ መካን መሆን ከአሁን ዘመን ይልቅ በማህበረሰቡም ዘንድ እንደ ትልቅ ጉድለትና እርግማን ተደርጎ የሚታይበትና የሚያስነቅፍ ስለ ነበር፡፡
  - በተለይም በባል ወላጆችና የቅርብ ዘመዶቹ ዘንድ የማትወልድ ሴት የማትፈለግ/የምትጠላ፣ ስለ ነበር፣ ባሏ እንዲፈታት ግፊት እንዲያደርጉበት በር ከፋች ምክንያት ሊሆን ስለሚችል፤
  - ብዙ ልጆች የምትወልድ ሴት በባል የምትወደድበት ጊዜ ነበር፣ ምክንያቱም በወቅቱ የሚሰራው ስራ ሁሉ በሰውና በእንስሳት ጉልበት ይሰራ የነበረበት ስለሆነ አባት በሚሰራው የጉልበት ስራ እንዲያግዙ ወንዶች ልጆች ይፈለጉ ስለነበር፣
  - ሐናና ባለቤትዋ አብረው ሲኖሩ ያፈሩት ሐብትና ንብረት እንዲሁም ርስት ካለ ወላጆቹ ሲሞቱ የእርሷ ዘር የሆኑ ወራሽ ልጆች አለመኖራቸው ሊያሳስባት ስለሚችል፤
  - እግዚአብሔር ዕድሜ ሰጥቷት ብዙ ዓመታት ኖራ በሽምግልና ደከምከም ስትል የሚጦራት ልጅ አለመኖሩ፤

- አንዱ ቤተሰብ ሰርቶ ያፈራው ሀብት ንብረት ካቅራቢያም ሆነ ከርቀት ጉልበተኞች መጥተው የሚዘርፉበት/የሚነጥቁበት ጊዜ ስለነበረና እንዳሁኑ ዘመን የጸጥታ ችግር ሲፈጠር 911 የሚደወልበት ስላልነበረ አባት በርከት ያሉ ወንዶች ልጆች ካሉት በቀላሉ እንዳይደፈርና እንዲመከት/ እንዲከላከል የሚያግዝ ስለ ነበር ነው፡፡ ንጉስ ሰለሞን እንዲህ ሲል የዘመረው ይህንኑ የሚያመለክት ነው፤

መዝ 127፡4-5፣ "በወጣትነት የተገኙ ወንዶች ልጆች ፣ በጦረኛ እጅ እንዳሉ ፍላጾች ናቸው፡፡ ኮረጆዎቹ በእነዚህ የተሞሉ የተባረከ ሰው ነው፤ ከጠላቶቻቸው ጋር በአደባባይ በሚሟገቱበት ጊዜ አይዋረዱም፡፡"

የእግዚአብሔር ባርኮት ወደ ህዝቡ እጅ የሚገባው በአብዛኛው በዘልማድ ይሆናል ተብሎ በሚጠበቅ ጊዜ ነው (ምሳሌ- ፍናና ባል እንዳገባች ልጆች መውለዷ፤) በዚህ ዓይነት ወቅቱን ጠብቆ ለመጣ በረከት ሁሉ ሰጪው እግዚአብሔርን ማመስገን ነው፡፡ እግዚአብሔር ለአንድ ሰው የሰጠው ስጦታ ባቅራቢያው ላሉት ሰዎች ከተሰጣቸው ስጦታ የበለጠ/የተሻለ ሲሆን በዚያ ስጦታ/በረከት እግዚአብሔርንና ሰዎችን ማገልገያነት መጠቀም ነው እንጂ፣ መታበያ/መኩራሪያና መመኪያ፣ አነስተኛ ስጦታ ያላቸውን መናቂያ ማድረግ በእግዚአብሔር ፊት ጸያፍ ነው፡፡ እግዚአብሔር የሰዎችን ስራ ሁሉ ይመዝናልና፤

አንዳንዴ በረከት ከሚጠበቀው ጊዜ ፈጥኖ/ቀድሞ ሰው እጅ ይገባል፡፡ (ምሳሌ፡ ድንግል ማርያም ገና ባል ሳታገባ ልጅ ጸንሳ መውለዷ፣ በአሁኑ ጊዜም ጥቂት የማይባሉ ሕጻናት በነብይነት ቅባት መቀባታቸው፤ (እንደዚያ ሲሆንልን እግዚአብሔርን እንደ ፈቃድህ ይሁንልኝ ማለት ነው)፣ አንዳንዴ ደግሞ ሊዘገይ ይችላል፣ (ምሳሌ፡ የሌዊ ዘር ባለቤት የሐናና፣ የነብዩ አብርሐም ሚስት የሳራ መካንነት፤ የያዕቆብ ባለቤት የራሔል መካንነት፣ የማርያምና ማርታ ወንድም አልዓዛር ታሞ ጌታ እንዲመጣላቸው ተልኮበት ሳይመጣ መዘግየት)፡- የእነዚህ ሰዎች በረከት ቅዱሱ ያዘገየው ለእነርሱ ያዘጋጀው በረከት ስላልነበረ/እንዲጎዱ ስለፈለገ አይደለም፡፡ እግዚአብሔር ለእነርሱ መልካም ዕቅድ ስለ ነበረው ነው፡፡ ግን መቼ/በምን ሁኔታ ቢሰጣቸው ታላቅ መልካምነቱን ይበልጥ እንደ ሚገልጥና እነርሱም እንዴት ዝነኛ የእግዚአብሔር ሰዎች ተብለው በዘመናት ሁሉ የሚታወቁ አድርጎ ሊያከብራቸው ስለ ፈለገ ነው፡፡ 1ሳሙ 2፡3 እግዚአብሔር አምላክ አዋቂ ነው አለች፡፡ ማለትም ሁሉም ነገር ያውቃል/የሚሰወርበት አንዳች ነገር የለም፡፡ እግዚአብሔር ምን ጊዜም የሚያደርገው ነገር ሁሉ ከሁሉ በተሻለ ጊዜና ሁኔታ ነው የሚያደርገው፡፡ ተሳስቶ የሚያደርገው ነገር የለም ማለት ነው፡፡ ከዘገየም ይዘገያል እንጂ እርሱ ያለው ነገር መምጣቱ አይቀርም፡፡

እግዚአብሔር በባህሪዋ ቅን ላልሆነችው ፍናና ልጆችን በጊዜው ሰጥቶ እንዴት መልካም ባህሪ ለነበራት ሐና አዘገየባት ሊያሰኝ ይችላል ሁኔታው፡፡ እግዚአብሔር ለአንድ ሰው ያለው እቅዱን ጨርሶ እስከሚገልጥ ድረስ አሰራሩን ሁሉ መረዳት ከባድ ቢሆንም እንደዚያ ያደረገበት ዋና ምክንያት የሚከተሉት ናቸው፤

1. በጎ ስጦታ ሁሉ ከእርሱ እንደሆነ እንዲታወቅ ነው፡፡

   1ሳሙ 1፡5-6 "...እግዚአብሔር ማሕጸኗን ዘግቶት ነበር፡፡ እግዚአብሔር ማህጸኗን ስለዘጋም ጣውንቷ ታስቆጣት ነበር፤ ይላል፡፡" ሐና ባል እስካላት ድረስ በራስዋ መውለድ ስትችል ሁሉን ቻይ የሆነው አግዚአብሔር የጾታ አካሏን አበላሸ/እንዳይሰራ አደረገ ማለት ነውን? በቅን ሰው ላይ ክፉ ማድረግ የእግዚአብሔር ባህርይ አይደለም፡፡ በሃና ላይ እንዴት ያልተገባ ነገር አደረገባት፡፡ ወይስ የቃሉ አተረጓጎም/ አረዳድ ላይ ምን ጉዳይ አለ ይሆን፡፡

በአራማይክ "ሳጌር ረኸም" የሚለው ቃል አንዳንድ ቅጂዎች እንድትወልድ አላደረገም ብለው ተርጉመውታል፣ ሌሎች ደግሞ ማህጸኗን ዘጋ ብለውታል፡፡ እንድትወልድ አለማድረግም ሆነ ማሕጸኗን መዝጋት የመጨረሻ ውጤቱ ልጅ አልባ መሆን ነው፡፡
ግን አሰራሩ ላይ ልዩነት አለ፡- ማህጸን መዝጋት ጤናማ በነበረው ማህጸን በራሱ ውስጥ ችግር/መዛባት መፍጠር ነው፤ እንድትወልድ አለማድረግ ግን የእርስዋን ማህጸን ጤናማነት ምንም ሳይነካ እግዚአብሔር የራሱ ድርሻ የሆነውን አላደረገም ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር ልጅ በመውለድ ሂደት ውስጥ የሚሰራው ምንድነው?

መዝ 127፡3፣ "እነሆ ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው፡፡ የማህጸንም ፍሬ ከእርሱ የሚገኝ ዋጋ/ሽልማት ነው፤"
ሕዝ 18፡4፣ "እነሆ ነፍስ ሁሉ የኔ ናት፣ የአባት ነፍስ የኔ እንደሆነች ሁሉ የልጁም ነፍስ የኔ ናት፡፡"
ዮሐ 3፡27፣ "ዮሐንስም እንዲህ ሲል መለሰ፤ ከላይ ካልተሰጠው በቀር ማንም አንዳች ሊቀበል አይችልም፤"
ያዕ 1፡17፣ "በጎ ስጦታና ፍጹም በረከት ሁሉ ከላይ ከሰማይ ብርሃናት አባት ይወርዳሉ…፤"
ዘካ 12፡1፣ "መክ 12፡7 አፈርም ወደ ነበረበት ምድር ሳይመለስ፣ ነፍስም ወደ ሰጠው እግዚአብሔር ሳይመለስ ፈጣሪህን አስብ፤"

ልጅ የሚወለደው ትዳር ስለያዙና የጾታ አካል ክፍሎች ጤናማ ስለሆኑ ብቻ አለመሆኑን እነዚህ ጥቅሶች ያሳያሉ፡፡ ስለዚህ ሃና ከእግዚአብሔር ብቻ የሚገኘው የልጅ ነፍስና መንፈስ ውስጣዊው ሰውነት በመስጠት እንድትወልድ ስላላደረገ፣ ሰላዘገየ ነው ልጅ ሳትወልድ የቆችው እንጂ ከማሕጸኗ ችግር አለመሆኑን ያሳያል፡፡

እንደ ሳይንስ ከሆነ እኔም ከመራባት ጋር የተያያዙ ትምህርቶች ተምሬያለሁ፡፡ ግን ሳይንስን ያስገኘው፣ ለሳይንቲስቶችም እውቀትን የሰጠው እግዚአብሔር ስለሆነ፣ ለኔ በሳይንስ እውቀት ላይ የእግዚአብሔር ቃል የበላይ ነው፡፡ ሳይንስ ነፍስና መንፈስን ሊመረምር አይችልም፡፡ በእጃችን የገባውም በረከት ሁሉ ከእግዚአብሔር እንደሆነ አውቀን ልናመሰግነው ይገባል (ተግተውና ብዙ ደክመው ስለሰሩ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር እርዳታ ሲደግፍ ነው የበረከት ወራሽ የሚኮነው፡፡
መክ 9፡11 (7፡13፣ 9፡1)፣ መዝ 75፡6-7

2. እግዚአብሔር ታምራት አድራጊ አምላክ መሆኑን እንዲታወቅ፤ እግዚአብሔር በየዘመናቱ/በየትውልዱ መልካም ስራ እየሰራ ራሱን ያለ ምስክር አይተውም ለብዙ ዓመታት ጽንስ ይዞ መውለድ ያልቻለ ማህጸን በጣም ቆይቶ እግዚአብሔር በፈቀደ ጊዜ ልጅ እንዲወልድ ማድረጉ እግዚአብሔር የተለመዱ ነገሮች ደጋግሞ የሚያደርግ ብቻ ሳይሆን በመለኮታዊ ኃይሉ ማድረግ የማይችለው ታምራዊ ስራ እንደሌለ ለዚያ ትውልድ ለማሳወቅ ነው፡፡ እኛ እግዚአብሔር በሙሴና በሐዋሪያት ዘመን ታምራት ማድረጉን ቢነገረንና አሁን በኛ ዘመን ምንም ታምራት ባያደርግ ምን ያህል እናምነው ነበር፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር በኔም ጉድለት/ችግር/ሕይወት ታምራት ያደርጋል ብለን አምነን መጠበቅ አለብን፡፡

3. ሁሉም በረከት ሰው በጠበቀው ጌዜ ሳይሆን እግዚአብሔር አንዳንዱን በራሱ ጊዜ የሚገልጥ/የሚለቅ ስለሆነ ነው፡፡ እግዚአብሔር ለሐና ተራ ያልሆነ፣ ለካህንነት የመረጠው ልጅ ሊሰጣት ዓለም ከመፈጠሩ በፊት አይቶላታል፡፡ ግን በእርሰዋ በኩር ልጅ ሳሙኤል ሊሰራ የፈለገው ስራ ለመጀመር የወሰነው ጊዜ ስላልደረሰ እርሷና ሌላ ሰው በጠበቀው ሰዓት ልጅ ስላላገኘች ነቀፌታ አስከትሎባት ሊሆን ይችላል፡፡

መልካም! እግዚአብሔር የሐናን ዘር ለፈለገው አገልግሎት መምረጡና ያን ልጅ የሚጠቀምበት የራሱ ጊዜ መወሰኑ ተገቢ ነው፡፡ እርሷ ይኽን ያህል እንዳትቸገር መጀመሪያ ሌሎች ልጆች ሰጥቷት ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ ልጇን ለምን አልተጠቀመም፣ ሊባል ይችላል፡፡
በሙሴ የክህነት ዘመን፣ እግዚአብሔር ለኔ አገልግሎት ይስጥ ብሎ ያስቀመጠው መመሪያ የበኩር ልጅን ነው፡፡ ስለዚህ ወላጆችም ሳይገደዱ ወይም ድንገት ሳይጠየቁ ራሳቸው አስበው በፈቃዳቸው ለእግዚአብሔር ስጦታ ብለው መስጠት የለመዱት የበኩር ልጅን ነበር፡፡
ለክህነት ስራ በማሰልጠን የሚያሳድግና የሚቀባ ካህን ያስፈልጋል፡፡ እግዚአብሔር ካህኑ ኤሊን ከእርሱ ልጆች ያልሆነ እገሌን ባንተ ቦታ ልተካው መርጨዋለሁና አስተምረህ አሳድገው ብሎ ሳያስደነግጠው እርሱና ልጆቹ አፍኒና ፊንሀስ ሳሙኤልን እንደ ጠላት ሳያዩት በፈቃደኝነት እንዲይዙት በማድረግ አሰልጥኖ ሾመው፡፡
በተለመደው/በጠበቁት ጊዜ ያላገኙት በረከት እግዚአብሔር ራሱ ሊሰራበት ባቀደውና ክብሩን ይበልጥ በሚገልጥ ሁኔታ ወይም የሚሳነው ነገር ምንም እንደሌለ ይበልጥ በሚያሳይ በራሱ ጊዜ ይገልጠዋል፡፡

4. ህዝቡ የተለያየ ችግር በገጠመው ጊዜ ማድረግ የሚገባውና የማይገበውን ለይቶ እንዲያውቅ ለማስተማሪያ፣

   እግዚአብሔር ባርኮትን ባያዘገይም በሌሎች የተለያዩ ምክንያቶች ሊዘገይ ይችላል፡፡ መካንነት ብቻ ሳይሆን ማንኛውም ዓይነት የበረከት ጉድለት በሰው ሕይወት ይከሰታል፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር እርሷን ብቻ ሳይሆን ማንኛውም የእግዚአብሔር ወገን የሆነ ሰው ችግር በገጠመው ጊዜ ማድረግ የማይገባውና ማድረግ የሚገባው ምን እንደሆነ ለይቶ እንዲያውቅ ማሳያ እንዲሆን ተጽፎ ተቀምጦልናል፡፡
   ሐና ልጅ መውለድ ባለመቻሏ ሰበብ ጣውንቷ ስታሸማቅቃት ታዝን፣ ታለቅስ፣ ትመረር፣ ትበሳጭ፤ ምግቧን መብላት ትተው ነበር፡፡ እነዚህን ሁሉ በማድረጓ የባሰ የራስዋን ሰውነት ጎዳች እንጂ ችግሯን አላሰወገደላትም፡፡ እኛ ከርሷ ተምረን እንደነዚህ ዓይነት ስህተቶች መድገም የለብንም፡፡

   ምን ነበራት፣ ምን ስትጨምርበት፣ ስታደርግ ነው እግዚአብሔር የጎበኛት? ከሐና ምን እንማራለን፤

   - በእግዚአብሔር ፊት በቅንነት እየተመላለሰች የኖረች ተወዳጅ የሆነ ለሌሎች መልካም ምሳሌ የሚሆን ባህርይ የነበራት ናት፡፡ 2፡3፣ "…እግዚአብሔር አምላክ አዋቂ ነው፣ ስራም ሁሉ በእርሱ ይመዘናል" አለች፡፡ መልካም ምግባሯን መዘነላት/አየላት/ወሮታም ከፈላት፡፡ በትውልዱ ሁሉ መልካም ምግባሯ ሲነገር እንዲኖር አከበራት፡፡ እግዚአብሔርን በሚያስደስት ሁኔታ ያወቅነውን የእግዚአሔር ፈቃድ በማድረግ ከኖርን ማናችንም ቢሆን በፊቱ ሞገስ እናገኛለን፡፡
   - ለፍናና ልጆች ስለተሰጣት አልቀናችም፣ ከፍናና የተሻለ በሆነላት ነገር ማለትም በህልቃና በመወደዷ አልታበየችም፡፡ ለወንድሞቻችንና እህቶቻችን መልካም በሆነላቸው ነገር መቅናትን፤ አንዳንድ በረከቶች ከሌላው የተሻለ ስለተሰጠን መታበይን ማስወገድ አለብን፡፡ የተለያየ በረከት የጎደላቸውን ሰዎች ከመናቅ ተቆጥቦ በሚቻለው መንገድ ሁሉ ማበረታታት የሁላችን ፈንታ ነው፡፡
   - ነቀፌታዋን/ውርደትዋን/ጉድለትዋን እየተናነቃት በመሸከም መቀጠል የለብኝም ብላ፣ ዝም በይ የሚሏትም ዝም አልልም ብላ ተነሳች፡፡ ከ10 ወንዶች ልጆች የሚበልጥ ባል ስላለሽ ይበቃሻል ስትባል እግዚአብሔር ለሁሉም ሰው የሚሰጠው የወል/የተለመደ ስጦታዬ ለማግኘት ማድረግ ያለብኝን ሁሉ ሳላደርግ አልተውም አለች፡፡ እግዚአብሔርም ብዙ ተባዙ፣ ምድርንም ሙሉዋት ነው ያለው እንጂ አንዳንዶቻችሁ ተባዙ አላለም፤ ዘፍ 1፡28፡፡

ጊዜያዊ ችግሮች ተገቢው እርምጃ በመውሰድ ካልተወገዱ ቋሚ ሆነው ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ተሸክመነው የኖርነው ችግር ሁሉ እግዚአብሔር እንደዚያው እንዲቀጥል ፈቃዱ ስላልሆነ ማድረግ ያለብንን ሁሉ በማድረግ የዘገየብንን በረከት ማስለቀቅ ይሻለናል፡፡

- ወደ እግዚአብሔር ጸለየች፤ እንዴት ጸለየች?
    1. ማንም ሌላ ሰው ሳትጨምር፣ ባሏም ተከተለኝ ሳትለው፣ አጠገቧ የነበረው የካህኑ ኤሊ ድጋፍ ሳትጠይቅ/ሳታማክረው ራሷ ወደ አምላኳ ጸለየች፤ በጸሎት የተፈለገውን ያህል ለመማጸን ተባባሪ ብታገኝ አይከፋም ነበር፤ ግን ብዙውን ጊዜ አይገኝም፤ እንደ ሐና፣ እኛ ራሳችን ብንጸልይ አምላካችን እንደ ሚሰማን ማወቅ አለብን፡፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሁላችንም አማኞች ወደ ሙሉ ሰው አድገን ብርቱ ተዋጊዎች እንድንሆን ነው እንጂ ሁሌ ድጋፍ ፈላጊዎች ደካሞች እንድንሆን አይደለም፡፡
    2. ችግሩ የመረራትን ያህል አብዝታ በማልቀስ (ከልቧ) ጸሎትዋ መሰማቱን እስኪታወቃት ድረስ ባለማቋረጥ በእምነት ጸለየች፡፡ ካህኑ ዔሊ ደጋግሞ ሲያያት ጸሎትዋን ስታስረዝም ነው ሰክራለች በሎ የጠረጠራት፡፡ በጸሎት የሚተባበሩ ሰዎች ሲጸልዩ፣ ጸሎትህ መመለሱን እስከሚታወቅህ ድረስ አብረውህ ለመጸለይ ጊዜ ላይኖራቸው ይችላል፡፡ ግን ባለ ጉዳዩ ለራሱ ጉዳይ ለመጸለይ በቂ ጊዜ ሊያመቻች ይችላል/ይገባዋል፡፡
    3. ድምጽዋን ሳታሰማ ጸለየች፡- ድምጽ በማሰማት መጸለይ የምትቸገሩበት ሁኔታ ካለ ድምጽ ሳያሰሙ የጸለዩት ጸሎት እግዚአብሔር እንደ ሚሰማ እርግጠኛ በመሆን ጸልዩ፡
    4. የጸሎትዋ ርዕሰ ጉዳይ አንድ ብቻ ነበር፡፡ አጥብቀን የጸለይንበት አንድ ጉዳይ መልስ ስንቀበል 2ኛው ጉዳያችን ላይ በሌላ ጊዜ መቀጠል ይቻላል፡፡ በጉባኤ ጸሎት ወቅት ግን ብዙ ጉዳዮች በአንድ ጊዜ በማካተት መጸለይ ይቻላል፡፡
    5. ከጸለየችም በኋላ በእምነት ስለቆየች ከዚያ በኋላ አላለቀሰችም፣ አላዘነችም፡፡ እግዚአብሔር ማህጸኗ በሐኪሞች ተቆርጦ ለወጣው ለቲቢ ጃሸዋ ሚስትም እንኳ ልጅ ሰጥቷታል፡፡
- ለምና የተቀበለችው ነገር መልሳ ለእግዚአብሔር ክብርና ለእግዚአብሔር ስራ ለመስጠት ወሰነችና ስዕለት ተሳለች፡፡ እግዚአብሔርም ጸሎትዋን ሰምቶ ፈጥኖ ልጅ ሰጣት፡፡ ያን ጊዜ ዘላቂ መፍትሄ አገኝታ ልጅ ታቀፈች፡፡ ከሚያሳቅቃት ነቀፌታ ተገላገለች፡፡
  የተሰጣትም ልጅ ገና ጡት እንደጣለ እጅግ በሚያባባ ጊዜ ሳትሳሳ ቃሏን ጠብቃ ለእግዚአብሔር ሰጠች፡፡

የሃና፣ ልጅ የመውለድ በረከት እግዚአብሔር በራሱ ዓላማ ለተወሰነ ጊዜ ያዘገየው እንጂ ከኃጢአትም ሆነ ከሌላ ጠላት ስራ ጋር ግንኙነት ያለው አልነበረም፡፡ እንደዚህ ዓይነቱ የበረከት መዘግየት በጣም አልፎ አልፎ በጥቂት የእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ የሚከሰት ነው፡፡ ነገር ግን በብዙ የእግዚአብሔር ህዝብ በረከት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያመጡ ሌሎች ነገሮች አሉ፡፡ እነዚህም የእግዚአብሔርን ቃል ባለመታዘዝ፣ በክፉ መናፍስት ተጽዕኖ፣ በረጋሚዎችና አስረጋሚዎች ሥራ… ወዘተ ሲሆኑ ሁሉም ለእግዚአብሔር ክብር እንደሚገባ በመኖርና ጠላቶችን በዕምነት ጸንቶ በመቃወም የሚወገዱ ናቸው፡፡